የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነትን ለማጓጓዝ የሚያስችል የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት የወጣ መመሪያ

# ቁጥር…/2017

ሀምሌ /2016
አዲስ አበባ

## መግቢያ

ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ሀገራት ካላቸው አመታዊ የጅዲፒ መጠን ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ እቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለማዘዋወር እና የንግድ እንቅስቃሴን ለማሳለጥ በእጅጉ ያግዛል ፡፡ በሀገራችን በሰፊው የተስፋፋው እና ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው የትራንስፖርት አይነት የመንገድ ትራንስፖርት ሲሆን ወደውጭ የሚላኩም ሆነ ከውጭ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ የተላያዩ አይነት እቃዎች በመንገድ ትራንስፖርት የሚጠቀሙ ናቸው፡፡

በሀገራችን እየመጣ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ በርዝመቱ፣ በወርዱ፣ በክብደቱ፣ እና በቁመቱ ምክንያት ከተሽከርካሪው የጭነት ስፖንዳ ውጭ ወጥቶ የሚረዝም አንድ ነጠላ ጭነት አይነት በሰፊው ሲጓጓዝ ይስተዋላል፡፡ ይህንን ግዙፍ የሆነ እቃ ለማጓጓዝ የምንጠቀማቸው ተሽከርካሪዎች በተሽከርካሪ ክብደት እና መጠን መወሰኛ ደንብ ቁጥር 491/2014 መሰረት የሚከለከል እና በመንገዱም ላይ ሆነ በሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እና አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ይህንንም መሰረት በማድረግ እንደዚህ አይነት ግዙፍ የሆኑ ያልተለመደ እና አደጋ ጭነት ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ የጭነት አይነቶች ካላቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር ወደሀገር ውስጥ ሲገቡ ሊጓጓዙበት የሚችሉበትን ሁኔታ እና አጠቃላይ አሰራር ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሚኒስቴሩ በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነትን ለማጓጓዝ የሚያስችል የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት የወጣ መመሪያ ቁጥር…/2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

1. **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
2. **"አገልግሎት"** ማለት የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ነው፤
3. **"ክልል"** ማለት በህገ- መንግስቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
4. **"የሚመለከተው አካል"** ማለት ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ መንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት እና የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ማለት ነው፤
5. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል
6. **"ያልተለመደ ጭነት"** ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ ከሚፈቀደው ከፍተኛ መጠን ወይም ልኬት በላይ የማይነጣጠሉ ጭነቶች ማለት ነው፤
7. **"ያልተለመደ ጭነት አጓጓዥ ተሽከርካሪ"** ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ ከሚፈቀደው ከፍተኛ መጠን ወይም ልኬት በላይ የማይነጣጠሉ ጭነቶችን የሚሸከሙ ተሽከርካሪዎች ወይም ተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤
8. **"አደገኛ ጭነት "** ማለት በተሽከርካሪ የሚጓጓዝ ሆኖ በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የተመደበ ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ የታመቀ ጋዝ፣ አሲድ፣ ዝገት ነክ ንጥረ ነገር፣ መርዛማ ቆሻሻ፣ ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር፣ የሬድዮ ሞገድ ማመንጨት የሚችል የንጥረ ነገር ወይም የጋዝ ባህሪ ያለው ዕቃ ነው፡፡
9. **"አጃቢ "** ማለት ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነቶች በሚጓጓዙበት ወቅት ከፊት እና ከኋላ በመሆን ደህንነትን ለማረጋገጥ፣የትራፊክ አስተዳደርን ለማመቻቸት እና አስፈላጊ ዕርዳታዎችን ለመስጠት እና ለማጀብ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እና ሰራተኞችን የሚያካትት ነው፡፡
10. "አሳጃቢ" ማለት ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነቶችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ የሚጠይቅ ተቋም ወይም ግለሰብ ማለት ነው
11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነቶች በሚጓጓዙበት ወቅት የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ መንገዶች ላይ ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነቶች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነቶች **አይነት እና አጫጫን**

## 5. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ዓይነቶች

1. ጭነቱ ከተሽከርካሪው የቀኝ ወይም የግራ ጎን ካለው አካሉ ከ15 ሴንቲሜትር (0.15 ሜትር) የበለጠ ከሆነ፤
2. ጭነቱ ከተሽከርካሪው ፊት እና ከበስተኋላው መጨረሻ ካለው አካሉ 1.25 ሜትር በላይ ከሆነ፤
3. የተሽከርካሪ፣ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ጠቅላላ ከመንገድ ከፍታው ጭነቱን ጨምሮ ከ4.60 ሜትር የሚበልጥ ከሆነ፤
4. ለተሽከርካሪዎች ወይም ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች የጫነው ከፍተኛ ክብደት ከ56 ቶን በላይ ከሆነ፤

5. በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የተመደበ ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ የታመቀ ጋዝ፣ አሲድ፣ ዝገት ነክ ንጥረ ነገር፣ መርዛማ ቆሻሻ፣ ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር፣ የሬድዮ ሞገድ ማመንጨት የሚችል የንጥረ  ነገር ወይም የጋዝ ባህሪ ያለው ከሆነ፤

**6. ያልተለመደ ጭነት** የሚያጓጉዙ **ተሽከርካሪዎች ዓይነት**

1. ጠቅላላ የጎን ስፋት ከፊት የውጭ በኩል ከቀኝ ጠርዝ እስከ ግራ ጠርዝ ወይም በተቃራኒው ተለክቶ 2.65 ሜትር የሚበልጥ ተሽከርካሪ፤
2. ያልተጣመረ ነጠላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ ከ12.50 ሜትር የበለጠ፤
3. የተጣመረ ተሽከርካሪ ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከነተሳቢው የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ እስከ ኋላው ጠርዝ ከ18.50 ሜትር የበለጠ፤
4. ተቀጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ጠቅላላ ርዝመት ከ22 ሜትር የበለጠ፤
5. ለተሽከርካሪዎች ወይም ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅሙ ከፍተኛ ክብደት 56 ቶን በላይ የሆነ፤

**6. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት አይነቶች**

ከተጠቀሰው መጠን በላይ ያላቸው የኮንስትራክሽን ማቴርያል ፣ ቅድመ ግንባታ ላይ ያሉ ተገጣጣሚ ቤቶች፣ ኮንቴነሮች፣ የማእድን ማውጫ መሳሪያዎች፣ የኢንዱስትሪ መሳሪያዎች፣ ወታደራዊ መሳሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ዕቃዎች፣ ተቀጣጣይነት እና መርዛማነት ያላቸው  እና ይህን የመሰሉ የጭነት አይነቶች፡፡

**7. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች የጥንቃቄ መርሆዎች**

1. ቀይ ባንዲራ (600*600ሚ/ሜ) ዳር ላይ የሚገኘውን የሎቤድ ተሽከርካሪውን ጠርዝ የሚጠቁም፤
2. የተሽከርካሪዎች ጋቢና ጠርዝ ላይ ብሩህ ቢጫ መልክ ያለው መብራት (ተንቀሳቃሽ ክሬን ከሆነ አንድ ከፊት ለፊት ሁለት ከኋላ )ያለው፤
3. የተሽከርካሪውን ጠርዝ በሚጠቁም መልኩ መብራት እና አንፀባራቂ መጠቀም፤
4. የፍጥነት ገደብ ሰሌዳ ወይም ቦርድ (400ሚ.ሜ ዲ ያሜትር) በሰዓት ከ60ኪ.ሜ ባነሰ ፍጥነት መጓዝ እንዳለበት ከዋርኒንግ ቦርዱ በላይ መሰቀል አለበት፡፡
5. ከተሽከርካሪው ፊት እና ኋላ በቀይ የተፃፈ በጉልህ የሚታይ (ABNORMAL LOAD) የሚል ሰሌዳ፤

**8. አጃቢ ተሽከርካሪዎች**

1. ከአደጋ ሊያስጠነቅቅ የሚችል ብርሃን ወይም አንፀባራቂ ያለው ልዩ ምልክት ሊኖራቸው ይገባል፤
2. ከተሽከርካሪው አናት በስተፊት ቀይ ወይም ሰማያዊ መብራት ወይም ተሽከርካሪው ወደ ኋላ በሚነዳበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በኋላው ነጭ መብራት የሚያሳይ ተሽከርካሪ መጠቀም አለበት፤
3. የተሽከርካሪው የተወሰነ አካል ክፍል በቀይ እና በቢጫ የሚያስጠነቅቅ አንፀባራቂ መሸፈን እና ያልተለመደ ጭነት (ABNORMAL LOAD) የሚል ምልክት ያለበት መሆን አለበት፣

4. ለእጀባ አገልግሎት የሚውሉ አንፀባራቂ ዱላዎች፣ ኮኖች የተሽከርካሪ ማቆሚያ ታፔላ፣ሶስት መአዘን አንፀባራቂ፣ አንፀባራቂ አልባሳት እና ሌሎችም ሊኖር ይገባል፡፡

**9. ስለማሳወቅ**

1. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የሚጭኑ አካላት ጭነቱ ከሚጫንበት ከ 10 ቀን በፊት ለሚኒስቴሩ፣ለአገልግሎቱ እና ለመንገዶች አስተዳደር ማሳወቅ አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እንዲያውቅ የተደረገው አካል ጭነቱ ስለሚጓጓዝበት ሁኔታ ዝርዝር እቅድ ያወጣል፣
3. በዕቅዱ መሰረት አደጋ በማያደርስ ሁኔታ ታጅቦ ዕቃው እንዲጓጓዝ ይደረጋል፤

## ክፍል ሶስት
## የተለያዩ አካላት ሀላፊነት

**10. የሚኒስቴሩ ሀላፊነት**

1. መመሪያውን ያፀድቃል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
2. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አካላት ምላሽ ይሰጣል፤
3. ከመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ እና ከመንገዶች አስተዳደር ጋር ተባብሮ በመስራት የእጀባ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
4. የመዘግየት ክፍያ(ዲመሪጅ ክፍያ) ባገናዘበ መልኩ ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች በቂ ዝግጅት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
5. የሚጓጓዙ እቃዎች ጥራት እንዳይበላሽ እና ጉዳት እንዳይደርስበት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲደረግ ያደርጋል፤
6. መንገዶች ላይ እና ሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲደረግ ያደርጋል፤

**11. የአገልግሎቱ ሀላፊነት**

1. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚፈልጉ አካላት በሚያቀርቡለት ጥያቄ መሰረት የእጀባ አገልግሎት ይሰጣል፤
2. ከሚኒስቴሩ እና ከሚያሳጅበው አካል ጋር በጋራ በመሆን የጉዞ እቅድ ያዘጋጃል በእቅዱም መሰረት ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲጓጓዝ ያደርጋል፤
3. ለእጀባ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎችን እና ለደህንነት መጠበቂያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እንደ አስፈላጊነቱ ያቀርባል፤

4. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች በቂ ዝግጅት ያላቸው እና ለአደጋ የማያጋልጡ መሆኑን ያረጋግጣል፤
5. ከሚኒስቴሩ፣ ከመንገዶች አስተዳደር እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡
6. ከፊት ለፊትና ከኋላ አቅጣጫ የሚመጣው ትራፊክ በጥንቃቄ እንዲያልፍ የማስጠንቀቂያ ምልክት ይሰጣል፤
7. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ከመጓጓዙ በፊት ጉዞ የሚደረግበትን የመንገድ ደህንነት መሰረት ባደረገ ሁኔታ ያረጋግጣል ፣
8. መንገዶች ላይ እና ሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጋል፤
9. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የጫነው ተሽከርካሪ በቂ የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ማድረጉን፣ አንፀባራቂ እና የማስጠንቀቂያ መብራቶች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
10. በተለያዩ መዋቅር ስር የሚገኙ የትራፊክ ተቆጣጣሪ አባላት እና ተቋማት ጋር በጋራ ተባብሮ ይሰራል፤
11. በመታጠፊያ፣ በኩርባ፣ እይታን በሚከለክሉ ቁልቁለታማና ደገታማ በሆኑ ቦታዎች በአጃቢ ተሽከርካሪዎች ለተላላፊዎች በቅድሚያ መረጃ ይሰጣል ፣
12. የመጓጓዣ ፍጥነት እንደጭነቱ መጠንና ከፍተኛ ለአደጋ የማጋለጥ ሁኔታ ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን ህጉን መሰረት በማድረግ እንዲጓዝ ያደርጋል፤

**13. የመንገዶች አስተዳደር ኃላፊነት**

1. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት የሚዛን አገልግሎት ይሰጣል፤
2. በመንገድ፣በድልድይ እና በሌሎች መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ያደርጋል፤
3. ያልተለመደ እና አደገኛ ጭነት የሚጓጓዝበትን የመንገድ ክፍል ይለያል እቅድ ያወጣል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንገድ ጠረጋ ስራ ያከናውናል፤

**14. ያልተለመደ እና የአደገኛ ጭነት አስጫኝ ኃላፊነት**

1. በሕግ ከተደነገገው የጭነት መጠን፤ ከፍታ፤ የጎን ስፋትና ክብደት በላይ የሆኑትን ጭነቶች ሳይፈቀድለት ወይም አጃቢ ሳይመደብለት አለማጓጓዝ፤
2. የሚጓጓዘው ያልተለመደ እና የአደገኛ ጭነት በተገቢው እና አስተማማኝ በሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ላይ በትክክል መጫኑን የማረጋገጥ፤
3. ያልተለመደ እና የአደገኛ ጭነቱ በሚያልፍባቸው የመንገድ ድልድዮች ለማለፍ መቻሉን የሚገልጽ ፈቃድና የመንገድ ላይ የኤሌክትሪክ ኃይልና ስልክ ገመዶችን ማለፍ መቻሉን ከሚመከለተው ተቋም ፈቃድ የማግኘት፤
4. ላልተለመደ እና ለአደገኛ ጭነቱ እጀባ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች እንደአስፈላጊነቱ የማቅረብ፤
5. ጭነቱ ወደ መዳረሻው የሚጓዝበትን የመንገድ መስመር (route) ቀድሞ ከሚኒስቴሩ እና ከአገልግሎቱ ጋር በመሆን በጥንቃቄ የመምረጥ፤
6. ከሚጓጓዘው ጭነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ማናቸውንም ሠነዶች አሟልቶ መያዝ፤

7. በአጓጓዥ ድርጅትና በጭነቱ ባለቤት መካከል ሕጋዊ የትራንስፖርት ውል እንዲኖር ማድረግ፤
8. የዴመሬጅ አዋጅና መመሪያን በማክበር ተግባራዊ ማድረግ፤
9. የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣ ለአጃቢዎች የውሎ አበል ክፍያን በወቅቱ ወጪ መጠን መክፈል፤
10. ስለተሰጠው አገልግሎት ግብረ መልስ መስጠት፤

15.**የአጓጓዥ ተሽከርካሪ ኃላፊነት**

1. በሕግ ከተደነገገው የጭነት መጠንና ክብደት በላይ የሆኑትን ጭነቶች ሳይፈቀድለት ወይም አጃቢ ሳይመደብለት አለማጓጓዝ፤
2. የጭነት መኪናው አሽከርካሪ ሕጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መያዙን ማረጋገጥ፤
3. የተሽከርካሪው ብቃት የተረጋገጠና የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤
4. በተሽከርካሪው የውጪ አካልና በጭነቱ ላይ የተሟላ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች መደረጋቸውን የማረጋገጥ፤
5. ጭነቱን እንዲያጅቡ የተመደቡት ሠራተኞች በሚሰጡት የጉዞ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ፣ ብልሽት ቢያጋጥም ለመጠገን የሚያስችል በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤
6. ከባለንብረቱ ጋር የገባውን ውል በማክበር መሥራት፤
7. አሽከርካሪና ወኪል ከሥራ ቦታው (ከተጫነው ጭነት) ሳያሳውቁ በፍጹም ርቀው እንዲሄዱ ያለመፍቀድ፤
8. ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ አሽከርካሪው የብቃት ማረጋገጫውን ለአጃቢው መስጠት ፤

16.**የእጀባ ሰራተኞች ኃላፊነት**

1. የጉዞ ዕቅድ አዘጋጅቶ በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግ፤
2. አጠቃላይ የትራፊክ ፍሰትን እና ደህንነትን የጠበቀ እንቅስቃሴ በተለይም በመስቀለኛ መንገድ አካባቢ እንዲኖር የማድረግ ፤
3. በትራንዚት ወቅት እንደ ሸክም ወይም ሜካኒካል ችግሮች ወይም ሌሎች ያልተጠበቁ ክስተቶችን የመቆጣጠር፤
4. በመንገድ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ መሰናክሎችን አስቀድሞ በመለየት የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤
5. አጠቃላይ የጉዞውን ሁኔታ በሚመለከት ለሚመለከተው አካል ያልተቋረጠ መረጃ የማስተላለፍ፤
6. ያልተለመደ እና የአደገኛ ጭነቱ መሪ እና የአደጋ ጠባቂ መሆን ይኖርበታል፣
7. የእጀባ ተሽከርካሪዎች የትራፊክ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር እና ያልተለመደ እና የአደገኛ ጭነቱን ለማጀብ ተብለው የተዘጋጁ የማጀቢያ ተሽከርካሪዎችን ብቻ መጠቀም ይኖርበታል፤
8. የጉዞው መነሻና ማታ ማብቂያ ሰዓት እንደተደራሹ ከተማ ሁኔታ ጥዋት መነሻ 12፡00 ሰዓት ሆኖ ማታ ከቀኑ እስከ 12፡30 የሚደረስባቸው ቦታዎች ብቻ እንዲሆን ያደርጋል፣

## ክፍል አራት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**17. አቤቱታ ስለማቅረብ**

በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፦

1. አገልግሎት በተሰጠው በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚመለከተው አካል ኃላፊ በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፤
2. የሚመለከተው የበላይ ኃላፊ አቤቱታው በቀረበለት በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ውሳኔውንም በጽሁፍ አድርጎ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤
3. አቤቱታ አቅራቢው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ አግባብ ላለው አካል ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

**18. የመተባበር ግዴታ**

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ፡፡

### 19.ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

### 20. መመሪያዉን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

**21. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ...... ቀን /2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ዓለሙ ስሜ(ዶ/ር)**

**የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚንስቴር ሚኒስትር**